# እንደ ሽሚዝ የሚቀያየር የፖለቲካ እምነትና አቋም

## ክፍል ሶስት
(ካለፈው የቀጠለ)

በሸዋይልማ ኪዳኔ (ጀርመን)

አንድ ፖለቲከኛ የአባላቱንና የደጋፊዎቹን ከዚያም አልፎ የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን ከበሬታና አድናቆት ማግኘት የሚችለው ለፖለቲካ እምነቱ በቆራጥነት ያለማወላወል ሲታገል እንደሆነ መናገሩ መድገም ካልሆነብኝ በስተቀር አዲስ ነገር እንዳልሆነ በሚገባ እገነዘባለሁ። ፖለቲካም ተለዋዋጭ ክስተት እንደመሆኑ የፖለቲካ እምነትም ሊለውጥ እንደሚችልም ጠንቅቆ ይገባኛል።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን የፖለቲካ እምነታቸውን እንደፈለጉ ለመቀየር የማይቸግራቸው፣ አቋማቸውን በሌላው ላይ ለመጫን የማይፈሩ፣ የፖለቲካ ድርጅትን ዝቅ አድርጎ እንደ ግልንብረትነት ለማየት የሚፈልጉ ፖለቲከኞችን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ዓይነቱ ፖለቲከኞች ፖለቲካን ቲያትር ያስመስሉታል። ጥያቄው ፖለቲከኞቻችንን ምን ያህል እናውቃቸዋለን? የሚል ነው። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይህን ጥያቄ ለመመልስ አንድን ፖለቲከኛ በምሳሌነት እንዲያቀርብ ይገደዳል። አስገራሚ የሆነ የአቋም መለዋወጥ ከሚታይባቸው “በተቃዋሚ የፖለቲካ ጎራ“ ውስጥ ከሚገኙ ፖለቲከኞች ውስጥ ከመድኅን ፓርቲ አንጃ በመፍጠር የተገለሉት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በአሁኑ ስዓት በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተጨማሪም በዚህኛው ክፍል ውስጥ ተመሳሳይ ችግር የሚታይባቸው አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ የተባሉ የቀድሞ የአርዱፍ ዋና ጸሐፊ የነበሩ ግለሰብ ድርጅታቸውንና የድርጅቱን ደጋፊዎች ከድተው የወያኔን አገዛዝ እውቅና አግኝተው ተለጣፊ አርዱፍ በመፍጠርና ራሳቸውን የድርጅቱ ሊቀመንበር አድርጎ በመሾም ትላንት ምን ይሉን እንደነበርና ዛሬ ደግሞ ምን እያሉን እንደሆነ ራሳቸውን እየጠቀስኩ በመጠኑም ቢሆን ሁለቱ ገጽታቸውን በአጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ።ታዋቂ ግለሰብ ፖለቲከኞቻችንን ከመደገፍም ይሁን ከመተቸት በፊት ማንነታቸውን እምነታቸውንና የዓላማ ፅናታቸውን ማወቁ የመጀመሪያው ተግባራችን ሊሆን ይገባል ባይ ነኝ።

## የአንድ ሰሞን ፖለቲካ

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለ9 ዓመታት ያገለገሉትን የደርግ መንግስት ከድተው ድምፃቸውን ካጠፉ በኋላ የደርግ ስርዐት መንገዳድገድ ሲጀምር የቀድሞ አለቃቸው የነበሩትን ርዕሰ ብሔሩን ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማሪያምን በኃይለኛ ቃላት እየተቹ ድምፃቸውን በአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ ማሰማት ጀመሩ። እንደገና ድምፃቸውን ለጥቂት ጊዜ አጥፍተው ከቆዩ በኋላ ወያኔ/ኢህአዴግ ወደ አዲስ አበባ እየተቃረበ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ሲቀሩት በኢዴሐቅ ውስጥ በግለሰብ ደርጃ አባል በመሆን እንደገና ወደ ፖለቲካ መድረኩ ብቅ አሉ። ኢዴሐቅን በግለሰብ ደረጃ በአባልነት ሲቀላቀሉና ለቀው ሲወጡ ስማቸው አንድ ሰሞን ሲነሳ እንደገና መልሶ ሲጠፋ ቆይቶ በመጨረሻ መድኅን ተመሠረተ። ጥቂት አገር ወዳድ ከሆኑ ኢትዮጵያውያኖች ጋር በመሆን መድኅን ተመስርቶ የመጀመሪያው የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆነው በመመረጥ በፖለቲካ መድረክ ላይ በመሪነት ብቅ አሉ። ለአጭር ጊዜ የፖለቲካ ፀጥታ ሰፍኖ ከኢዴሐቅ መሪዎች ጋር እንካ ሰላንቲያ መግጠም ሲጀምሩ እንደገና የፖለቲካ መድረኩን ያዙት። እንካ ስላንቲያውም አብቅቶ የፖለቲካ ፀጥታ ሰፈነ።

ያ ሁሉ የፖለቲካ ስድብና አሽሙር ግዜውን ጨርሶ ጥቂት ፀጥታ ሰፈነ ሲባል የመድኅን አመራርና የድርጅቱ አባላትን ሳያሳውቁ በካሴት አስቀርፀው ለኢትዮጵያ ህዝብ የላኩት የክተት ጥሪ የዚያን ሰሞን የመነጋገሪያና የመወያያ አጀንዳ ሆነ። በጊዜው ፋሽን ቢጤ ስለነበር ኮ/ል መንግስቱም ካሉበት ከሐራሬ ሆነው ወደ አምስት ካሴት የሚሆን ንግግራቸውን አስቀርፀው ለኢትዮጵያ ህዝብ በትነው ስለነበር አሜሪካን አገር አንዳንድ ሱቅ ውስጥ ሳይቀር ይሸጥ እንደነበር በጊዜው ሰምቻለሁ። እንደገና ለረጅም ጊዜ ድምፃቸውን አጥፍተው ከቆዩ በኋላ በመድኅን ውስጥ አንጃ ፈጥረው የአንጃው መሪና ፕሬዝዳንት ተብለው መድኅንን በጠረኝነት እየከሰሱ ራሳቸውን የሰላም አርበኛ በማድረግ እንደገና ወደ ፖለቲካ መድረኩ ብቅ አሉ። በመቀጠልም ከሐምሌ 19 እስከ 26 ቀን በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የተካሄደውን የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ ላይ የጥላቻ ዘመቻ በማካሄድ የህዝብ ስሜት የሚያቆስል የጥላቻ ፖለቲካ ማካሄድ ጀመሩ። በዚያን ሰሞን የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ሁኔታ ያላስገረመው ሰው ማግኘት ያስቸግር ነበር። መልሶ ደግሞ ፀጥታ ቢጤ ሰፍኗል።ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለረጅም ጊዜ በሚስጥር ከወያኔ ባለሰልጣናት ጋር ሲደራደሩበት የነበረው ጉዳይ አደባባይ ወጥቶ ሰላማዊ ትግል የሚል ሽፋን ተሰጥቶት የወያኔን አስተዳደር እውቅና በማግኘት የሚመሩት ቡድን ስርታፊኬት ካገኘ ውሎ አድሯል።ታዲያ ፕሬዚዳንቱ የሚመለሱት መቼ ነው ብለን እንጠይቅ ይሆናል። መልሱ በጣም ቀላል ነው። በሌላ በኩል ለኮ/ል ጎሹ ወልዴ የደህንነት ዋስትና ለማግኘት የዲፕሎማሲ ስራ እየተሰራ ነው በማለት ኮ/ሉ በወያኔ ተለጣፊነት እንዳይታሙ ሌላ ቲያትር እየተዘጋጀልን ነው። ጫወታው ሁሉ ተጨፈኑና እናሞኛችሁ መሆኑን የሚነግሩን ከሆነ እኔ በበኩሌ አይኔን ለመጨፈን ዝግጁ ነኝ። በእውነቱ እኔ በግሌ ሳይበዛ እንዲህ

ዓይነቱን የአንድ ሰሞን የፖለቲካ ቲያትር ማየት ደስ እንደሚለኝ ከአንባቢ መደበቅ አልፈልግም። አልፎ አልፎ እንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ቲያትር በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ባይኖር ኖሮ ፖለቲከኛውም ህዝቡም ፖለቲካ እሬት እሬት ባለው ነበር።

## እጅና እግር የሌለው ፕሮፓጋንዳ

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ተቀምጠው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የመምከራቸው ዜና መተላለፍ ከጀመረበት ሰዓት ጀምሮ አብሮ ለብዙዎቻችን እንግዳ የሆነና ፈጽሞ ስምተን ከማናውቀው ተቀማጭነቱ ዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ውስጥ ከሆነው " የኢትዮጵያዊነት ድምፅ" ሬዲዮ ጣቢያ ከመድኅን በአንጃነት ከተገነጠለው የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን ጋር በማበር በዋሽንግተኑ የተቃዋሚዎች ኮንፈረንስ ላይ የማጥላላት ዘመቻ ማካሄድ መጀመሩን የተለያዩ የግሉ ፕሬስ ውጤቶች ለሕዝብ አሳውቀዋል። ይህን የጥላቻ ፖለቲካ ዘፕሬስ በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ ሲዘግብ፦

> *" ... የኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ይህን ስብሰባ (የሁሉም ፓርቲዎች ኮንፈረንስ) የኢሕአፓ አቋም የሚንፀባረቅበት ከመሆኑም በላይ የሌሎችን ተሳትፎ የሚያንኳስስ ነው እያለ በመግለጽ ወደ ስብሰባው የሚሄዱትን ሁሉ ይህን ከግምት ውስጥ እያስገቡ አሊያም በስብሰባው እንዳይካፈሉ ቅስቀሳ እያከሄደ ነው። "*
>
> *ሐምሌ 9 ቀን 1995 ዓ.ም*
>
> *ዘፕሬስ*

ዓይኔ ያየውን ለማረጋገጥ የግድ የኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያን መስማት ስለነበረብኝ ከኮንፈረንሱ መጀመር በፊት፣ ከተጀመረ በኋላና የህብረት ግንባሩ በተመሠረተ ማግስት የተላለፉት ፕሮግራሞችን በማዳመጤ ጆሮዬ ዓይኔ ያየውን ዜና እውነታ አረጋግጦልኛል። በእውነቱ ፕሮፓጋንዳውን የሰማ ሁሉ ራሱን ታዲያ የወያኔ ካድሬዎች ምን ሠርተው ይብሉ ብሎ እንዲጠይቅ ያስገድደዋል። እኚሁ የኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ "ጋዜጠኛ" የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን የኢንቴርነት ሬዲዮ ላይም ከኮ/ሉ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ በመስማቴ ለምን በፕ/ር ስዩም ገላዬ የሚመራውን መድኅንን እንደሚጠሉ እንድገነዘብ የረዳኝ ሲሆን በኮ/ሉ ቡድን ውስጥም ዘነጋሁት ብቻ የህዝብ ግንኙነት ይሁን ወይም የድርጅት ጉዳይ እንደተሾሙ ስምቼአለሁ።

*መቶ አለቃ ምርጫው ሁለት ነገሮችን እንዲገነዝቡልኝ አስቀድሜ እጠይቃለሁ። የመጀመሪያው ከላይ እንደጠቀስኩት የግሉ ፕሬስ ስለ እርሶ የዘገበው በሙሉ እውነት ሆኖ ስላገኘሁት ሳልተችበት ማለፍ አለመፈለጌን ሲሆን ሁለተኛው ትችቱ የሚያተኩረው ከላይ በተጠቀሰው ጊዚያት ውስጥ ማለትም የሁሉ አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔን፤ ጉባዔው የፈጠረውን የህብረት ግንባርና መድኅንን በተመለከተ (በኮ/ል ጎሹ ወልዴ በሚመራው የአንጃው የኢንቴርነት ሬዲዮ ላይ በቡድኑ አባልነቶ በመድኅን ላይ ያስተላለፉትን ፕሮፓጋንዳ አይመለከትም) "የኢትዮጵያዊነት ድምፅ" ሬዲዮ ጣቢያን በመጠቀም ሲነዙት በነበረው ፕሮፓጋንዳ ላይ ብቻ ያተኮረ ትችት እንጂ ከዚህ በፊት የማላውቀውን ስራዎትን በሙሉ የማይመለከት መሆኑን እንዲያውቁልኝ እፈልጋለሁ።*

በእውነቱ እኔ በግሌ በእርሶ ላይ ፈረንጆቹ " Old Wine, new Bottle " የሚሉት ባህሪ በግልጽ ይታየኛል። *መቶ አለቃ ምርጫው በደርግ ዘመን የኢሠፓ ወታደራዊ ካድሬ በነበሩበት ጊዜ ምን ያህል የተዋጣሎት ካድሬ እንደነበሩ የማውቀው ነገር የለም። በእውነቱ የማወቅ ፍላጎቱም የለኝ። በዚህ በኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያዎ ለማስተላለፍ የሚምክሩት ፕሮፓጋንዳ ወይም በትክክለኛ ስሙ ልጥራውና የማጥላላት ዘመቻ ግን ፈጽሞ አልሰራም። ስለሆነም ነው ስሞ በግሉ ፕሬስ ላይ በመልካሙ ያልተነሳው። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከእርሶ ጋር ባደረጓቸው ቃለ ምልልሶች ውስጥ እንደዚያ እርር ድብን እያሉ በእልህ በህብረቱና መድኅንን ጨምሮ በአንዳንድ የህብረት ግንባሩ አባል ድርጅቶች ላይ ያላቸውን ጥላቻ የሚገልጹት በእሳቸው ፕሬዝዳንትነት የሚመራውና እርሶም በአባልነት የሚገኙበት የመድኅን አንጃ ቡድን በኮንፈረንሱ ላይ ባለመጋበዙና ከሁሉም በላይ ኮ/ል ጎሹ ለስምና ለዝናቸው እጅግ በጣም አጥብቀው የሚጨነቁ ግለሰብ በመሆናቸው ዛሬ የደረሰባቸው የፖለቲካ ክስረት የፈጠረው ንዴትና ብሽቀት ሊሆን እንደሚችል ለማንም ግልጽ ይመስለኛል። የእርሶን ግን ምን ብለን እንጥራው?*

*መቶ አለቃ ምርጫው የአንጃውን የኢንቴርነት ሬዲዮ ለፕሮፓጋንዳ፣ የኢትዮጵያዊነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያን በዋሽንግተን ዲሲ ከተማና በአካባቢው ለሚኖረው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ እርስ በእርስ የሚማማርበት፣ ሃሳቡን የሚለዋወጥበት መድረክ፣ ምሁራኖችን በመጋበዝ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ኢትዮጵያዊያኖች ያላቸውን ግንዛቤ የሚያሳድጉበትና የእኛ የሚሉት የሬዲዮን ጣቢያ እንዲኖራቸው ከማድረግ ይልቅ ወይ ከሕዝቡ ጎን ቆመው የህብረቱ ግንባር በመመሰረቱ እንደ ሕዝቡ አልተደሰቱ አሊያም ከወያኔ ጋር ሆነው የጎሳ ፖለቲካ አልዘፈኑ እንዳው በመሃል ሜዳ ራስዎትን ዝቅ አድርገው ለጥቂት ግለሰቦች በመሳሪያነት በማቅረብ ከነዚህ ግለሰቦች ተጽፎ የሚቀርብ ጽሑፍ በማንበብና ትዕዛዝ በመቀበል የሌሎች አፍ ሆነው የኢትዮጵያዊነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያን ለሌሎች የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ እንዲሆን በማድረግ ማጋልጋሎ የሚያሳዝን ነው። እርሶ " በገንቢ ትችት" ሽፋን ሊያስተላልፉልን የሚሞክሩት መልዕክት በይዘቱም ሆነ በቅርጹ ኮ/ል ጎሹ በተቃዋሚዎች ህብረት ላይ እና በህብረቱ አንዳንድ አባል ድርጅቶች ላይ ከሚሰነዝሩት የጥላቻ ፖለቲካ በምንም መልኩ አይለይም። አንድን ትችት ገንቢ ትችት ከሚያሰኙት መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ለምንተቸው*

አካል ካለን ፍቅርና ተቆርቋሪነት በመነሳት በምናቀርበው ጠቃሚ ሃሳብ እንዲጠናከር ካለን ፍላጎት በመነሳት ከሆነ ብቻ ነው። በእውነቱ ገንቢ ትችት ምን እንደሚመስል ለማወቅና ለመማር ከፈለጉ እዚያው እርሶ በሚኖሩበት አገር ነዋሪ የሆኑትን የዶ/ር ግርማ በቀለን ጽሑፎች እየፈለጉ ያንብቡ። እርሶ እንድዚያ ሊያጥላሉት የሞከሩትን የተቃዋሚ ኃይሎች ኮንፈረንስን ወያኔ እንኳን ሊያንቋሽሸው ፈጽሞ አልሞከረም። በመሆኑም የመለስ መንግስት ኮንፈረንሱን በሚመለከት የተናገረውን ሪፖርተር ሲዘግብ፦

> *" … ከሐምሌ 19 እስከ 23 ቀን 1995 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ የሚካሄደው የተቃዋሚ ቡድኖች የጋራ ጉባዔ ላይ እንድንካፈል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቀረበለት ጥሪ አለመኖሩን ኢህአዴግ ገለፀ። … "*
>
> *ሐምሌ 14 ቀን 1995 ዓ.ም*
> *ሪፖርተር*

ብሎ ነበር። በአጭሩ መ/አለቃ ምርጫው ፕሮፓጋንዳውን ፈጽሞ የቻሉበት አልመሰለኝም። ፕሮፓጋንዳ አንድን አመለካከት ለመደገፍ ወይም ለመጉዳት ሆን ተብሎ የሚሰነዘር የሃሰት መረጃ፣ ሃሳብ ወይም አሉባልታ ሲሆን ደጋፊዎችን ለማግኘት ሲባል የሚሰራጭ የሃሰት ፖለቲካ ነው። የናዚዎችን ታሪክ በመጠኑም ቢሆን ለሚያውቅ ሰው የአዶልፍ ሂትለር የፕሮፓጋንዳ ሚኒስተር የነበረው ዶ/ር ጆሴፍ ጎብልስ ምን ያህል የተሳካለት ፕሮፓጋንዲስት እንደነበር ማወቅ ይቻላል። ዶ/ር ጎብልስ ሂትለርን የጀርመንን ህዝብ ልብና አመኔታ እንዲያገኝ ካስቻሉት ባለስልጣኖች ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው። በእውነት ገነትና ሲኦል ያለ ከሆነ የጎብልስ ነብስ ሲኦል ውስጥ እንዳለች ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም። የምፈራው ግን ያቺ ምላሱ አብራው ከነብሱ ጋር ሲኦል ውስጥ ካለች ግን ብዙውን አሳስታ ከገነት ወደ ሲኦል እንደምታስገባ የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም። እኔ የእርሶን የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ አብዛኛውን ሰምቻለሁ። እርሶን ሚጢጢው ጎብልስ ብዬ ልጠራዎ አልፈልግም። ምክንያቱም ሙገሳ ይሆንብኛልና። ሆኖም ግን እንደዚያ ሌት ተቀን በኢትዮጵያዊነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያ ላይ ሲደክሙለት የነበረው የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን ደግፌ ባያስገኙለትም እንዲያው ለድካሞ ሲል ግን እርሶን ሚጢጢው ጎብልስ ብሎ ቢጠራዎት አያንሶትም ባይ ነኝ። ዛሬ ደግሞ ያ ሁሉ ድካሞ ተረስቶ በእርሶና በኮ/ሉ የሞቀ ግንኙነት ላይ ቀዝቃዛ ውሀ ፈሶበታል ይባላል። አሁንም ቢሆን በያዙት የሬዲዮን ጣቢያ ላይ በሚገባ ሕዝቡን በማገልገል ከተጠቀሙበት ስሞትን ለማደስና መልካም ስም ለማግኘት እድሉ አሎት ባይ ነኝ።

## <u>መድኅን፣ አርዱፍና ኢዴኃን - የወያኔ ሰለባዎች</u>

የወያኔ አስተዳደር በተለያዩ ጎሳዎች ስም የጎሳ ድርጅቶችን በመፍጠር ኢህአዴግ የሚባል ግንባር ፈጥሮ በፈላጭ ቆራጭነት የወያኔን ፖሊሲ ሲያስፈፅም እንዳልነበር ዛሬ ደግሞ ወያኔ ራሱ ከዚያ ዝቅ ብሎ አቶ መለስ ዜናዊ እንዳፈለጋቸው የሚያዙበት ድርጅት ለመሆን በቅቷል። ወያኔ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ከሚጠቀምበት ዘዴዎች ውስጥ ዋነኛው ተለጣፊ ድርጅቶችን በመፍጠር በአንድ በኩል የተባበረ ጠንካራ የተቃውሞ ኃይል እንዳይኖር በማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ የተለያዩ ድርጅቶች በአገሪቱ ውስጥ ያሉ በማስመሰል የዓለም አቀፍ ህብረተሰብን ድጋፍ ለማግኘት ይረዳው ዘንድ ለይስሙላው ዴሞክራሲ ይጠበቅባቸዋል። ከዚያም አልፎ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች ተቃውሞ እንዳይገጥማቸው ይረዳው ዘንድ ተለጣፊ የሙያ ማህበራትን በመፍጠር ቢንቀሳቀስም የፖለቲካ ድርጅቶቹን ያህል በሙያ ማህበራቱ ዘንድ ፈፅሞ አልተሳካለትም።

ዛሬ ወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶችን የመፍጠሩን ሞያ ይበልጥ ተክኖበት እውነተኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ሳይቀር ሰርጎ በመግባት ትላንት በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ የነበራቸውን ፖለቲከኞች በተለያዩ ዘዴዎች በመቅረብና በማባበል፣ አንዳንዶቹም ራሳቸው ቀርበውት ትላንት ይወክሉት በነበረው የፖለቲካ ድርጅት ስም የደንብና የፕሮግራም ማስተካከል በማድረግና አዲስ ዓርማና ማህተም ቀርፀው በሕጋዊ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ የተቃዋሚ ኃይሎችን የሚያዳክምና የሚከፋፍል እስትራቴጂ ቀይሶ የስልጣን ዘመኑን የሚያራዝም አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ቢባል ማጋነን አይሆንም። እስኪ የወያኔ አገዛዝ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ እና አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስን በመጠቀም በመድኅንና በአርዱፍ ውስጥ አንጃ እንዲፈጠር በማድረግ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ተለጣፊዎችን በመፍጠር ተለጣፊ የኢዴኃንን ለመፍጠር የጀመረውን ጉዞ አብረን እንመልከት።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ አስቀድመው የወያኔን አስተዳደር አዎንታ በሚስጥር አግኝተው ስለነበር በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ለሚገኘው የምርጫ ቦርድ የፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት የጻፉትን ማመልከቻ አስይዘው ከአውሮፓ የላኩት ግለሰብ ማመልከቻውን ባስገባ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቡድናቸው እውቅና አግኝቶ ሰርታፊኬት አገኘ።ታዲያ ወያኔ በሌሎቹ እውነተኛ የተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ምነው ጨከነ ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ ሌሎቹ የኮ/ሉን መንገድ ስላልተጓዙ ብቻ ነው የሚል ይሆናል። ኮ/ል ጎሹ ራሳቸው የስደት ፖለቲካቸውን ጨርሰው „አገር ውስጥ ገብተው በሰላማዊ መንገድ" መንቀሳቀስ ሳይጀምሩ የቀድሞ ድርጅታቸው መድኅንን የስደተኞች ፓርቲ በማለት ስያጥላሉት ስሰማ በጣም ይገርመኛል። የስደት ፖለቲካ (Diaspora Politics) በኢትዮጵያ ብቻ የተጀመረ አዲስ ነገር እንዳልሆነ የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም። በስደት አገር የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች አገር ውስጥ ካሉት ጋር በመጣመርም ሆነ ለብቻቸው በምርጫ በመካፈል

የፖለቲካ ስልጣን የያዙባቸውን የአፍሪካ አገሮች መጥራትም ይቻላል። በተለይም ግሎባላይዜሽን ለስደት ፖለቲካው ተጨማሪ አቅም እንደሰጠው አሌ አይባልም። በመሆኑም ከአገራቸው ርቀው የሚኖሩ ዜጎች የሚያምኑበትን የፖለቲካ አመለካከት አገር ውስጥ ላሉ ዜጎች ለማካፈልና ድጋፋቸውን ለማግኘት ግሎባላይዜሽንም ሆነ የቴክኖሎጂው ዕድገት የቱን ያህል እንዳገዛቸውና በዚህ ረገድ ትናንት የነበረባቸውን ችግር ምን ያህል እንዳቃለለላቸው የምናየው ጉዳይ ይመስለኛል። ዛሬ የኢዴፓን የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የግድ አንድ ጣራ ሥር መቀመጥ የለበትም። ስለሆነም ኮ/ል ጎሹ ወልዴና አንዳንድ እንደ እሳቸው የሚያስቡ ግለሰቦች ተቃዋሚዎች ከአገራቸው ርቀው ስለሚገኙ ብቻ በአገራቸው የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ምንም ተጽዕኖ አያሳድሩም ብሎ ማመን ከፍተኛ ስህተት ይሆናል። ስለሆነም በስደት ላይ የሚኖሩ ዜጎች በቡድንም ሆነ በተናጥል አገር ውስጥ ካሉ ወገኖች ጋር በቀላሉ መገናኘትና ሐሳብ መለዋወጥ ስለሚችሉ ወደደም ጠላ በመንግስት ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀሬ ነው። ቁም ነገሩ ተጽዕኖው ለአገሪቱ የሚጠቅም እንዲሆን ማድረጉ ላይ ነው። በመሆኑም ሚስጥሩ የገባቸው የጋናና የናይጄሪያን መሪዎች ጨምሮ የአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች መንግስታት በስደት የሚኖሩ ዜጎቻቸው በአገራቸው የፖለቲካ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ በጎ ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችል እስትራቴጂ ንድፈው የሚንቀሳቀሱ በመሆኑ መሪዎቹ ለጉብኝት በሚሄዱባቸው አገሮች ውስጥ ዜጎቻቸውን እየሰበሰቡ የማነጋገሩ ባህል እየተጀመረ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም ወደ አገራችሁ ተመልሳችሁ ኢንቨስት አድርጉ፣ በሙያችሁና በእውቀታችሁ፣ አገራችሁን እርዱ የተለመዱ ቋንቋዎች ሆነዋል።

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን በወያኔ አስተዳደር የምርጫ ቦርድ በጠየቃቸው መሠረት የስልት ብቻ ሳይሆን የእምነትና የዓላማ ለውጥ ለማድረጋቸው ምልክት የሆነውን የፕሮግራም የደንብና የአርማ ለውጥ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ የሰጣቸው መሆኑንና ወደፊት ከሌሎች የተቃዎሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ እንደ ኮ/ል ጎሹ ወልዴና አቶ ማሃሞዳ አህመድ ጋስን የመሳሰሉ ግለሰቦችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን የምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ተጠባባቂ ሬጅስራር የሆኑት አቶ መኮንን ወንድሙ ሲገልጹ፣-

> *"...የትጥቅ ትግል አማራጭ ትቶ በሠላማዊ የምርጫ መድረክ ለመወዳደር ያለውን ፍላጎት በፕሮግራሙ መድረክ ለመወዳደር ያለውን ፍላጎት በፕሮግራሙ በግልጽ መቅረጽ እንዳለበት ተነግሮት በእንቅስቃሴው ላይ ችግር እንዳይፈጠር ሁሉም አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉለት ከቦርዱ የትብብር ደብዳቤ እንደተጻፈለት ቦርዱ በሠላማዊ መድረክ በምርጫ ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸውን አዲስም ሆነ ነባር የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅም በፈቀደ መጠን ከመደገፍ ወደኋላ እንደማይል ጨምረው ገልጸዋል። ..."*

ጥር 3 ቀን 1996ዓ.ም
*ሪፖርተር*

የመድኅን ፓርቲ በድርጅቱ ላይ ስለተፈፀመበት ክህደትና በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚመራው ቡድን አዲስ ማህተምና አርማ ቀርፆ፣ የደንብና የፕሮግራም ለውጥ አድርጎ የወያኔን አስተዳደር ዕውቅናና ድጋፍ አግኝቶ በስሙ ለመንቀሳቀስ የሚያደርገውን ጥረት በማውገዝ ባወጣው መግለጫ ላይ በሁለቱ መሀከል ያለውን ልዩነት ሲያስረዳ፣-

> *"...ቀደም ሲል የስልት እንጂ የዓላማ ለውጥ የለንም እያለ ያዙኝ ልቀቁኝ ይል የነበረውና በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚመራው ከመድኅን የተገነጠለው አንጃ ሰሞኑን የአርማ ለውጥ በማድረግ ማንነቱን ግልጽ አድርጓል። በሰላም ትግል ስም ለኢትዮጵያ ሕዝብ „ብርቅዬ የክፉ ቀን ልጆችህ መጣንልህ" እያሉ ቀዳዳ ከበሮ ማስመታታቸው መጨረሻው ሀገር ቤት ለመመዝገብ የከፈሉት ደጅ መጥኛ ቢሆንም የአርማና የዓላማ ለውጥ ማድረግ ስለነበረባቸው እነሆ በወያኔ ታሽቶና ተስተካክሎ በወያኔም አመለካከት ተሰርዞና ተደልዞ የተሰጣቸውን አርማና ዓላማ በመቀበል ይኸው „አገር ቤት ተመዘገብን" በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በገሀድ ይታለል ይመስል መጣንልህ (መጣንብህ) ብለዋል። ..."*

የካቲት 17 ቀን 1996 ዓ.ም
*የመድኅን ፓርቲ ጋዜጣዊ መግለጫ*

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት በመድኅንና በአንጃው መካከል ያለው ልዩነት የዓላማና የስልት በመሆኑ ሕዝቡም ሁኔታው ጠንቅቆ ስለገባው አዲስ አበባ ውስጥ ሳይቀር መድኅን ቁጥር አንድና ሁለት እየተባሉ የሚጠሩት ያለምክንያት አይደለም። መድኅን ቁጥር አንድ የድሮው በዓላማውና በእምነቱ ፀንቶ የቆመውና በፕ/ር ስዩም ገላዬ የሚመራው መድኅን ሲሆን መድኅን ቁጥር ሁለት ደግሞ አዲሱና በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚመራው የገዢውን ዕውቅና ያገኘው „መድኅን" እየተባሉ እንደሚጠሩ ሰምቻለሁ። በቅርቡ ፍራንክፈርት ከተማ ውስጥ በኢዴፓን የድጋፍ ኮሚቴ ተጠርቶ በነበረው ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ አዲሱን ህብረት በመወከል በስብሰባው ላይ ተገኝተው ለነበሩ የህብረቱ ተወካዮች ስለ መድኅን ከአንድ ተሳታፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ በህብረቱ ውስጥ ከእኛ እየሰራ ያለው በፕ/ር ስዩም ገላዬ የሚመራው መድኅን ነው። በመቀጠልም በሁለቱ መሀከል የአርማ፣ የደንብና የፕሮግራም ልዩነት እንዳለ ስለሰማንና ስለምናውቅ እንግዲህ በመሃከላቸው ያለው አንድነት የስም ሞክሼነት ብቻ ነው በማለት ነበር የመለሱት።

ሌላው በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ፣አድናቆትና ዝናን ያተረፈው በአቶ ሞሃመድ ኢብራሂም የሚመራው የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ) እና በአፋር ሕዝብ ዘንድም ኡጉጉሞ በመባል የሚታወቀው ድርጅት ላይ የአቶ መለስ ዜናዊ አስተዳደር ተለጣፊ ለመፍጠር የተጠቀመው

የአርዱፍን ዋና ፀሓፊና የድርጅቱ የአውሮፓ ተጠሪ የነበሩትን በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታና አድናቆት የነበራቸውን አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስን መሆኑ ብዙ ኢትዮጵያዊያኖችን አሳዝኗል። አቶ ማህሞዳ ጋስ ትላንት እጅግ በጣም ተወዳጅና የሕዝብን አመኔታ አግኝተው ከነበሩ ጥቂት የተቃዋሚ ፖለቲከኞች ውስጥ አንድ የነበሩ ናቸው።አርዱፍ አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ ድርጅቱን ከድተው በድብቅ ወደ አዲስ አበባ መገባታቸውን ድርጅቱ እኤአ በኦክቶበር 21 ቀን 2002 ዓ.ም ባወጣው መግለጫው ላይ ጠቅሶ አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ ድርጅቱን ፈጽሞ የማይወክሉ መሆኑን በጊዜው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳውቆ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። አቶ ማህሞዳ ጋስ በደርግ ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸውና የአሰብ አስተዳዳሪ ራስ ገዝ ክልል የኢሠፓ አንደኛ ፀሐፊ ሆነው ያገለገሉና ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ልምድ ያላቸው ግለሰብ ናቸው።

አርዱፍ ወያኔና ሻዕቢያ አጥብቀው የሚፈሩት ጠንካራ ድርጅት እንደሆነ የድርጅቱን ታሪክ በመጠኑም ቢሆን የተከታተለና የሚከታተል ሰው የሚያውቀው ጉዳይ ይመስለኛል።በመሆኑም ወያኔና ሻዕቢያ የጦር ኃይላቸውን በማስተባበር በተደጋጋሚ ድርጅቱን ለማጥፋት ያደረጉት ሙከራ ሊሳካላቸው አልቻለም። አቶ መለስ ዜናዊ ከሚስተር ኢሳያስ አፈቀርቂ ነሐሴ 10 ቀን 1989ዓ.ም ለተጻፈላቸው ደብዳቤ መልስ ሲሰጡ፣

> *“... የኡጉጉሞ (ARDUF) የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ርዝራዦች በአካባቢው የፋጠርነውን ሰላም እያደፈረሱብን ስለነበር እንርሱን ለማባረር ተንቀሳቅሰናል። ...“*

ሚ/ር ኢሳያስ አፈወርቂ ደግሞ ለአቶ መለስ ዜናዊ ነሓሴ 19 ቀን 1989 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ ላይ፣

> *“... ኡጉጉሙን (ARDUF) በተመለከት እርምጃው ከመወሰዱ በፊት የየራሳችንን መከላከል እንድናደርግ ባሳወቅናቹህ መሠረት የኛዎቹም ለመተጋገዝ በሚቀርቡበት ወቅት ነው እርምጃ የወሰዳችሁት።...„*

ብለው ነበር።

ወያኔና ሻዕቢያ አርዱፍን ለማጥፋት ሲያድርጉት የነበረውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማረጋገጥ ከዚህ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረግ የሚያስፈልጋን አይመስለኝም።

ወያኔ አርዱፍን በኃይል ለማጥፋት ያደረጋቸው ጥረቶች በሙሉ አልሳካ ስላሉት የቀረው አማራጭ ከድርጅቱ ጋር መደራደር ብቻ ነበር። ከዚህ መረዳት የምንችለው ቁም ነገር ቢኖር አንድ ድርጅት ይዞት የሚነሳው ዓላማና ግብ የሕዝብን ፍላጎትና ጥቅም መሠረት ያደረገ ከሆነና የዚያ ሕዝብ ድጋፍ  እስከ አልተለየው ድረስ እንደዚህ ዓይነቱን ትግል የሚያቆም ምንም ኃይል ሊኖር አለመቻሉን ነው። የወያኔ አገዛዝ ከአርዱፍ ጋር በሚስጥር ድርድር አካሂዶ ደርጅቱን አባብሎ ወደ አገር ቤት ለማስገባት ያደረጋቸው ጥረቶች በሙሉ ያልተሳኩት በራሱ በወያኔ ግትር አቋሞቹ ሲሆን በተለይም ድርጅቱ የአሰብን ጥያቄ እስከ አላነሳ ድረስ እውቅና ሊሰጠው ባለመፈለጉ ብቻ ነው። ስለሆነም ወያኔ ሌላ ታክቲክ መጫወት ግድ ስለሆነበት የአፋርን ሕዝብ የትግል ስሜት ለመምታት የሓሰት ፐሮፓጋንዳውን ሥራዬ ብሎ ተያያዘው። የወያኔ/ኢህሓደግ አስተዳደር በሓምሌ ወር 1986 ዓ.ም በቁጥጥሩ ሥር በሚገኘው የመገናኛ ብዙሃን ከአርዱፍ ጋር ስምምነት አደረኩ ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብን ሲዋሽ፣

> *“...ሕገ መንግስት ከሚፈቅደው ውጭ ትጥቅ ይዞ በአፋር ክልላዊ መንግስት የሰላምና የልማት እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ሲፈጥር የቆየው የፖለቲካ ድርጅት አርዱፍ ወደ ሰላማዊ መድረክ መመለሱን አስታወቀ። ...“*

የሚል የሐሰት ዜና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አስተላልፎ ነበር። አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ ትላንት እጅግ በጣም ተወዳጅ ከነበሩና አመኔታ ካገኙ ጥቂት የተቃዋሚ ፖለቲከኞች ውስጥ አንዱ እንዳልነበሩ ዛሬ አዲስ ዓርማና ማህተም አስቀርፀው፣ የፐሮግራምና የደብን ለውጥ አድርገው፣ ድርጅታቸውን ከድተው፣ ራሳቸውን ሊቀመንበር ብለው ሹመው በአስተዳደሩ ታግዘው በድርጅታቸው ላይ ተለጣፊ አርዱፍ ፈጥረውት „ድርጅታችን የትጥቅ ትግል አቁሞ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ወሰነ“ ብለው በአደባባይ ሲዋሹ የሚመለከት አገር ወዳድ ዜጋ ገና ለገና ነገ ደግሞ የወያኔ አስተዳደር ከተቃዋሚው ጎራ ሊፈለፍል የሚችላቸውን ብዙ አቶ ማህሞዳ አህመዶችንና ኮ/ል ጎሹ ወልዴዎችን ሲያስብ የሚተርፈው ነገር ቢኖር ራስ ምታትና ተስፋ መቁረጥ ምናልባትም ከሁሉም በላይ በፖለቲካ ላይ እምነት እስከማጣት ቢደርስ እንኳን ሊገርመን አይገባም። አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ ትላንት ስለ ተለጣፊ ድርጅቶች በአደባባይ ሲያወሩ የነበረውን ፖለቲካ የሰማ ሰው ዛሬ ተለጣፍ አርዱፍ በድርጅታቸው ላይ ፈጥረው የወያኔ መገልገያ መሳሪያ ይሆናሉ ብሎ እንኳን በእውኑ በሕልሙም አያስበውም። አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ ትላንት ስለ ተለጣፊ ድርጅቶችና ስለ የወያኔ አገዛዝ የፖለቲካ ክስረት በአደባባይ ሲያስተምሩን፣-

> *“... የኢህሕዴግ መንግስት የፖለቲካ ክስረት ደርሶበታል። በአፋር አካባቢም ሆነ በመላው ኢትዮጵያ ኢህሕዴግ በፖለቲካ መስክ ተሸንፏል ለማለት ይቻላል። የተለጣፊ ድርጅቶች ስልት አልሰራም። በምርጫ አሸነፈ ተብሎ የአፋርን ክልላዊ መንግስት ያቋቋመው የአፋር ተለጣፊ ድርጅት አካባቢውን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር አልቻለም። በፖለቲካ ትግል ላይ የተሰማሩት የአፋር ተቃዋሚ ድርጅቶችና በትጥቅ ትግል ላይ የተሰማራው አርዱፍ በየአካባቢው ሕዝቡን ይዘው ኢህሕዴግ የመሰረተውን የአፋርን ክልላዊ መንግስት ሽባ በማድረግ ላይ ናቸው። ...አርዱፍ ማላት አላማ ነው።   የኢህሕዴግ መንግስት ከአርዱፍ ጋር የደረሰበት ስምምነት የለም። በእኔ አስተሳሰብ ስምምነት ላይ መድረስ ቀርቶ፣ ልዩነቶቻችን የሚጠብ ሳይሆን እየሰፋ የሚሄድ ሆኗል። ... የኢህሕዴግ መንግስት ከትዕዛዝ መልስ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ለድርድር አቀረበ። እነሱም መሳሪያችሁን*

*አስቀምጡ፣ በኤርትራ ያላችሁን የግዛት ጥያቄ እንድታንሱ፣ አለዚያም የኢትዮጵያን ግዛት ለቃችሁ ወደ ኤርትራ ግዛት እንድትሄዱ የሚሉ ነበሩ። …"*

አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ
መስከረም 11ቀን 1990 ዓ.ም
ከአንዲት ነፃ ኢትዮጵያ ድምፅ የሬዲዮ አገልግሎት እና
ከቀስተ ደመና የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ
ጋር ካደረጉት ቃለ ምልልስ የተወሰደ

አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ አርዱፍ ከወያኔና ከሻዕቢያ ጋር እያደረገ ያለውን ትግል በተለይም ከሻዕቢያ ጋር የሚያካሂደው የትጥቅ ትግል የጀመረው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም መሆኑን ጠቅሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግስት መለዋወጥ ትግሉን ሳያቆመው እስከ ዛሬ መዝለቁ በራሱ የአፋር ህዝብ ለብሔራዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ መከበር የሚያደርገው ትግል እውነተኛነትን በመጥቀስ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሓፊ ለሚ/ር ኮፊ አናን በፃፉት ደብዳቤ ላይ በኢትዮ-ኤርትራ የሰላም ስምምነት ላይ አርዱፍ ያለውን አቋምና በተለይም የድርጅታቸውን ትግል አስመልክቶ ሲገልፁ፣

*„The fact that the armed resistance of the Afar people has so far survived the fall and rise of regimes in Ethiopia explains and testifies its true nature as a popular nationalist movement. Over the last decade, since 1991, the Afar people have paid very heavily in their struggle to reinstate their national and demokratic rights. "*

*25 May 2001*
*Mohamoda Ahmed Gaas*
*Secretary General of ARDUF*

ትላንት አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ የአርዱፍ የትጥቅ ትግል ትክክለኛነት በመግለፅና ከወያኔና ሻዕቢያ ጋር የሚደረገውን ትግል ፍትሓዊ መሆኑን በየመድረኩ ላይ ለሕዝብ ስያስረዱ እንዳልነበርና በተለይም ለአፋር ሕዝብና ለአርዱፍ ኤርትራ ማለት ከዙላ ባህር ሰላጤ በላይ የሚገኝ መሬት እንደነበር እና ደንከልያ (የአፋር የቀይ ባህር ዳርቻ ክልል) ከተቀረው የአፋር ክልል በህግ የተዋሃደ የኢትዮጵያ ግዛት አካል ነው በማለት የእራሳቸውንና የድርጅታቸውን እምነት በየአገሩ እየዞሩ ለኢትዮጵያዊያኖች በመግለጽ ብቻ ሳይወሰኑ በተለይም አሰብን አስመለክቶ ከላይ በጠቀስኩት ደብዳቤያቸው ላይ ለተመድ ዋና ፀሓፊ ሳይቀር በማስረዳት የአፋር የቀይ ባህር አካባቢ ደንከሊያ እኤአ በ1998 ዓ.ም ከኤርትራ ክፍለ ሃገር ተለይቶ በአፋር የራስ ገዝ ክልል ተጠቃሎ ተጠሪነቱ ለማዕከላዊ የኢትዮጵያ መንግስት የነበር በመሆኑ በኤርትራ የተካሄደው ሪፈረንደም የቀይ ባህር ዳርቻ ክልልን የማይጨምር መሆኑንና 1900, 1902 እና 1908 የቅኝ ግዛት ውሎች በ1952 የኤርትራ በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር መጠቃለል ውድቅ የሚያደርጋቸው መሆኑን በመዘርዘር ሚ/ር ኮፊ አናንን ጭምር ለማሳመን ሲሞክሩ እንዳልነበር ዛሬ በወያኔ አስተዳደር እቅፍ ሥር መውደቃቸው ከላይ የጠቀስኳቸውን የግል እና የቀድሞ ድርጅታቸውን እምነት ሳይቀር በመለወጥ ተለጣፊ አርዱፍ ፈጥረው በመንቀሳቀስ የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት እየተጠቀሙበት ያለው መንገድ ራሳቸውን ካልሆነ በስተቀር ማንንም ሊያታልል እንደማይችል ሕሊናቸው ሊስተው እንደማይችል ግልጽ ነው።

ተለጣፊውን አርዱፍ ፈጥረው መንቀሳቀስ ከጀመሩ በኋላ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳውን በማሰራጨት ከፍተኛ ትብብር እያደረገላቸው የሚገኘው የወያኔ የድርጅት ንብረት የሆነው የዋልታ የኢንፎርሜሽን ማዕከል በመሆኑ በአሳይታ ከተማ ውስጥ የተካሄደውን የተለጣፊውን አርዱፍ የይስሙላ ጉባዔ አስመልክቶና በተለይም አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ „ድርጅቱን የትጥቅ ትግሉን አቁሞ ወደ ሰላማዊ ትግል እንዲመለስ" ያደረጉትን አስተዋጾ ሲገልጽ፣-

*"…የአፋር አብዮታዊ ዴሚክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ) ከትጥቅ ትግል ወደ ሰላማዊ ትግል መሸጋገሩ መልካም አስተዳደርን ለመፍጠር እንደሚረዳ…አቶ ሞሀሞዳ አህመድ ጋስ ለጉባዔው ተሰብሳቢ አርዱፍ ሲያካሂድ የቆየውን የትጥቅ ትግል ባለፈው ግንቦት 1995 ዓ.ም በመቆም ወደ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምዕራፍ በመሸጋገር የአፋር ሕዝብ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን መብትና ድሎች ጠብቆ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ በመሆን የበኩሉን ድርሻ ድርጅታቸው ለመወጣት መዘጋጀቱን ገልፀዋል።…የግንባሩ ሊቀመንበር አቶ ሞሀሞዳ አህመድ ጋስ ግንባሩን ከትጥቅ ትግል ወደ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ ለማምጣት ያደረጉት ጥረት የሚደነቅ መሆኑን የጉባዔው ተሳታፊዎች አስረድተዋል።…"*

ጥር 16 ቀን 1996 ዓ.ም
ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል

እዚህ ላይ አንባቢዬ እንዲገነዘበው የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር የመለስ አስተዳደር ስለ አርዱፍ የሚያሰራጫቸው ፕሮፓጋንዳዎች እርስ በርስ የሚጋጩ መሆናቸው በራሱ የሚተላለፉት ዜናዎች መረጃ ሊሆኑን ይችላሉ። በአንድ በኩል ወያኔ ከአርዱፍ ጋር ስምምነት ማድረጉን አስቀድሞ ከዘጠኝ ዓመት በፊት ነግሮን ነበር። በሌላ በኩል ራሳቸው አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ አሳይታ ከተማ ውስጥ ጥር 14 ቀን 1996 ዓ.ም በክልሉ መንግስት በመታገዝ በጠሩት የይስሙላ ጉባዔ ላይ ድርጅታቸው የትጥቅ ትግሉን አቁሞ የሰላማዊውን ትግል ከጀመረ ዓመት ያስቆጠረ መሆኑን ይነግሩናል። በመሀከሉ ደግሞ ፕሮፓጋንዳውን በማሰራጨት እያገዛቸው ያለው የወያኔው የፕሮፓጋንዳ ማሺነሪ የሆነው የዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ደግሞ 95 ከመቶ ያህል የሚሆኑ

የአርዱፍ ታጣቂዎች ወደ ሰላማዊ ኑሮ መመለሳቸውን አስመልክቶ በአፋር ክልል ዞን 2 በረህሌ ከተማ በአርዱፍ ታጣቂዎች ዙሪያ ለመነጋገር የተዘጋጀውን ዜና አስመልክቶ ባስተላለፈው ዜና ላይ፣

> *"...በአፋር ክልል ሲንቀሳቀሱ ከነበሩት የአርዱፍ ታጣቂዎች መካከል 95 በመቶው ወደ ሰላማዊ ህይወት መመለሳቸውን የክልሉ ምንግስት አስታወቀ። የአርዱፍ ታጣቂዎች ወታደራዊ አዛዥ የነበሩት አቶ ሳላህ ዓሊ ሁዳይ በስብሰባው ላይ እንደገለጹት፣ በኤርትራና በኢትዮጵያ የሚገኙ አፋሮች አንድ ናቸው በሚል ሃሳብ ድርጅታቸው ጦር አደራጅቶ ሲንቀሳቀስ መቆየቱን ገልፀው፣ ሕዝቡ ወደ ሰላማዊ ህይወት መመለስ እንዳለብን በጠየቀው መሠረት እጃችንን በሰላም ሰጥተናል ብለዋል።..."*

የካቲት 3 ቀን 1996 ዓ.ም<br>
ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል

ሠረዝ የእኔ ነው። እንግዲህ እዚህ ላይ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ቢኖር አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ የኤርትራን አፋሮች ኢትዮጵያዊነት መካዳቸው በራሱ በአርዱፍ ላይ ተለጣፊው ድርጅት ፈጥረው ለመንቀሳቀስ የሚያደርጉትን ጥረት እርቃን የሚያስቀረው መሆኑን ነው። ከሁሉም በላይ የአቶ ማህሞዳ አህመድ ጋስ ተለጣፊው አርዱፍ ከሕጋዊውና በአቶ ሞሃመድ ኢብራሂም ከሚመራው አርዱፍ ጋር ከስም ሞክሼነት በስተቀር ምንም ዓይነት የዓላማም ይሁን የእምነት አንድነትና ተመሳሳይነት የሌለውና እሳቸውም ትናንት ይከተሉት የነበረውን እምነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የቀበሩት መሆናቸውን መገንዘብ እንችላለን።

ኢዴኃን ሌላው የወያኔ ሰለባ ነው። የወያኔ አገዛዝ ህብረቱን ከፈጠሩት 15 ድርጅቶች ውስጥ በመድኅንና በአርዱፍ ላይ ተለጣፊ በመፍጠርና ሕጋዊ እውቅና በመስጠት ኢዴኃንን ለማድከም በረቀቀ ዘዴ እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ ሞያ በልብ ነው እንዲሉ በግልጽ በአዳባባይ ላይ ህብረቱን ሲያጥላላ የማንሰማው አለምክኒያት አይደለም። በሌላ በኩልም ኢዴኃንም የወያኔ አስተዳደር ሊያፈርሰው ከፈተኛ በጀት መድቦ በስውር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠንቅቆ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) የአመራር አባል የሆኑት ወ/ሮ አልማዝ ሰይፉ ከኢትዮጵ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ ሲናገሩ፣

> *"... የህብረቱ ጉባዔ እንዳይሳካ ይፈልጉ የነበሩ ወገኖች የኢሕአፓን ስም ይዘው የጉባዔውን ዓላማ ለማደናቀፍ ሞክረዋል። በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ አስተባባሪነት ጭምር ጉባዔውን ለማሰናከል አፍራሽ ግብረ ኃይሎች አገረ አሜሪካ ድረስ የፖለቲካ ትውስት ይዘው ተንቀሳቅሰዋል።...ሌሎች ደግሞ ለምን እኛ በሕብረቱ ውስጥ አልገባንም የሚሉ ፓርቲ ነን ባዮችም ግብረሃይሉ አጋዥ ሆነው ተንቀሳቅሰዋል።..."*

ወ/ሮ አልማዝ ሰይፉ<br>
ጳጉሜን 5 ቀን 1995 ዓ.ም<br>
ኢትዮጵ

እኔ በግሌ ኢዴኃን ራሱን ከጥቃት ለመጠበቅ ሲንቀሳቀስ አይታይም ባይ ነኝ። ይህን የምለው ያለ ምክኒያት አይደለም። በኢዴኃን መለስተኛ ፕሮግራም ውስጥ በቁጥር 4 ላይ የህብረቱን ተግባርና ኃላፊነት አስመልክቶ በንዑስ ቁጥር 4.3 ላይ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች አባላት የሆኑ የፖለቲካ እስረኞች ለማስፈታት የጋራ ትግል ያደርጋል ይለናል።ኢዴኃህ በአባል ድርጅቶቹ ላይ ወያኔ ተለጣፊዎች ፈጥሮበት እያለ ሕዝቡን ከውዥንብር ለማዳን በማሰብ እንኳን የኅብረቱ አባል ድርጅቶች የሆኑት በፕ/ር ስዩም ገላዬ የሚመራው መድኅንና በአቶ ሞሃመድ ኢብራሂም የሚመራው አርዱፍ መሆናቸውን በመግለጽ ራሱን ለመከላከልና ሕዝቡም ግንዛቤ ያገኝ ዘንድ እንዲረዳው በማሰብ ግማሽ ገጽ የምትሆን ጋዜጣዊ መግለጫ እንኳን ማውጣት ያልቻለ የህብረቱ አባል ድርጅቶች ፖለቲከኞች ሲታሰሩ ታግሎ ያስፈታል ብሎ ማሰብ ይቸግረኛል። የአንድ ህብረት ጥንካሬና ድክመት ከሚላካባቸው የተለያዩ መንገዶች ውስጥ አንዱ አባል ድርጅቶችበሚኖራቸው ጥንካሬና ድክመት እንደሆን ለማንም ግልጽ ነው። የወያኔ አገዛዝ ዛሬ በያዘው ተለጣፊዎችን የመፍጠር ፍጥነቱ ከቀጣለ ኢዴኃንን ክሎነን (cloning) ለማድረግ የቀሩት 13 ድርጅቶች ብቻ መሆናቸውን ህብረቱ ሊገነዘብ ይገባዋል።

## ሠላማዊ ትግል

ኢዴኃን በሐምሌ 28 ቀን 1995 ዓ.ም ባወጣው የአቋም መግለጫ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የመለስ አገዛዝን በሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል ከሥልጣን ለማስወገድ የወሰነ መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳውቋል። ኮ/ል ጎሹ ወልዴም እንዲሁ ከህብረቱ ጥቂት ቀደም ብለው አገር ውስጥ ገብተው ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ የወሰኑ መሆናቸውን በይፋ ከማሳወቅ አልፈው በምርጫ ቦርድ የፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ያቀረቡትን ማመልከቻ አይቶ በሕጋዊ መንገድ መንቀሳቀስ ይችሉ ዘንድ መዝግቦ የእውቅና ሠርቲፊኬት ማግኘት ችለዋል። ከአገር ውጪ የሚገኙ የተቃዎሚ ኃይሎች በአገር ውስጥ በሕጋዊ መንገድ እንዳይንቀሳቀሱ እንቅፋት የሆነው ማነው ? የተቃዎሚ ኃይሎች ከሰላማዊ የትግል ስልት ውጭ የሆነ አማራጭ እንዲከተሉ የሚያስገድዳቸው ማነው ? አንድ የተቃዎሚ የፖለቲካ ድርጅት ምን ዓይነት የትግል ስልት መከተል እንድሚገባው አቅጣጫውን የሚጠቁመው በስልጣን ላይ የሚገኘው ገዢው ፓርቲ እንደሆነ የሚስተው ያለ አይመስለኝም።እንግዲህ ኮ/ል ጎሹ ወልዴና ኢዴኃን በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል መወሰናቸውን የሰማ ማንም ግለሰብ ታዲያ በሁለቱ መሀከል ያለው ልዩነት ምንድነው የሚል አግባብነት ያለው ጥያቄ ማንሳቱ የማይቀር ነው። ይህን ጥያቄ በቀጥታ ከመመለሴ በፊት አንባቢዬ ሙሉ ስዕል ያገኝ ዘንድ ወደኋላ በመመለስ እግረ መንገዴን አንዳንድ ጉዳዮችን ለማንሳት እፈልጋለሁ።

ነሓሴ 1 ቀን 1988 ዓ.ም በተካሄደው የመድኅን ሶስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ፐ/ር እጅጉ ደምሴ የፓርቲው ሊቀመንበር ሆነው በመመረጥ ኮ/ል ጎሹ ወልዴን ከተኩበት ጊዜ ጀምሮ ኮ/ሉ ከአደባባይ ፖለቲካ እስከ ሚያዚያ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ርቀው ቆይተዋል። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከሰባት ዓመት በላይ ድምጻቸውን አጥፍተው ከቆዩ በኃላ ወደ አደባባዩ ፖለቲካ የተመለሱት አገር ውስጥ ገብተው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል የወሰኑ መሆናቸውን በማሳወቅ ነበር። አንድ ግለሰብ በፈለገው መንገድ ለመታገል የመወሰን መብትና ነፃነቱ የተጠበቀ መሆኑ ቢታወቅም የኮ/ል ጎሹ ወልዴ አቋም ግን በብዙዎች ዘንድ ብዙ መልስ የማናገኝላቸው ጥያቄዎችንና መላምቶችን መፍጠሩ አልቀረም።ምናልባት ኮ/ል ጎሹ ወልዴን በቅርብ የሚያውቁ አንድ ከአሜሪካን ለዕረፍት ወደ ኢትዮጵያ የሄዱ ሰው እንደተናገሩት ከሆነ፣

> *"... የኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሰላማዊ ትግል አርበኝነት እምነታቸውን ከመቀየራቸው ጋር የተያያዘ ነው። ባለቤታቸው ከሞቱባቸው በኃላ ከኦርቶዶክስ አማኝነት ወደ ፕሮቴስታንት ተከታይነት የተሸጋገሩት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ አሜሪካ በሚገኙ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ስብከት ያደርጋሉ፣ ወያኔን በፀሎት ማጥፋት እንደሚቻል ይሰብካሉ።..."*

ነሓሴ 7 ቀን 1995 ዓ.ም
ኢትዮጽ

ብለውን ነበር። ሌሎችም እንደዚሁ ብዙ ብለዋል። ኮ/ል ጎሹ ወልዴም አቋማቸው በብዙዎች ዘንድ ጥያቄ ማስነሳቱን በመገንዘባቸው ለዚህ ጥያቄ (ከአደባባይ ፖለቲካ ራሳቸውን ለረጅም ጊዜ ካራቁ በኋላ ወደ ፖለቲካ የተመለሱበትን ሁኔታ አስመልክቶ ሲጠየቁ)መልስ ለመስጠት በማሰብ በመቶ አለቃው ምርጫው በኩል በኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ በኩል እንዲጠየቁ በማድረግ በብዙዎች ዘንድ ተነስተው የነበሩ ጥያቄዎችን የማይመልስ እርስ በርሱ የሚጋጭ መልስ በመስጠት የሚከተለውን ብለውን ነበር።

> *"... ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ሙሉ በሙሉ ራሴን ያገለልኩ አይመስለኝም። የሀገሬን የፖለቲካም ሆነ አጠቃላይ ሁኔታ ከመከታተል ያቋረጥኩበት ጊዜ አልነበረም።  ልጆቼን ማሳደግ፣ ማስተማርና መንከባከብ፣ ከእነርሱ ጋር መሆን፣ መዋል፣ መጫወትና መጠበቅ እውነተኛ  የአባት ሃላፊነትና ግዳጅ አድርጌ ስለወሰድኩ ከፖለቲካም ሆነ ከሌሎች ጊዜ ተሻሚ ከሆኑ ተግባሮች ገለልና ሰብሰብ ብዬ እንድኖር ተገድጄ ነበር። ..."*

ነሓሴ 4 ቀ 1995 ዓ.ም
ኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ

እኔ ብዙ ሰዎች ከሚመቷቸው መላምቶች ይልቅ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚሉትን ሙሉ በሙሉ መቀበሉን እመርጣለሁ። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ራሳቸውን ከኢትዮጵያ ፖለቲካ አርቀው ነበር ብዬ ፈጽሞ አላምንም። ወደ ቁም ነገሩ ልመለስና የኮ/ል ጎሹ ወልዴ በሰላማዊ መንገድ አገር ውስጥ ገብቶ የመታገል ፍላጎት እሳቸው ሊያሳምኑን እንደሚፈልጉት በጥቅምት 9 ቀን 1995 ዓ.ም ተጸንሶ በየካቲት ወር 1996 ዓ.ም የተወለደ አዲስ የትግል ምዕራፍ ሳይሆን ከመድኅን ዕውቅና ውጭ በሚስጥር ከወያኔ አስተዳደር ባለሥልጣናት ጋር የተካሄደ ድርድር ውጤት መሆኑን ለማሳየት ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን ማንሳቱ አስፈላጊ ይሆናል። በመጀመሪያ ደረጃ ኮ/ል ጎሹ ወልዴን ከወያኔ ባለሥልጣናት ጋር በማቀራረቡ ረገድ ፓስተር እገሌ(ስም ላለመጥቀስ) ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። የመድኅን ፓርቲ የስ/አ/ኮሚቴ ከሚያዚያ ወር 1992 ዓ.ም ጀምሮ በሳምንት ሁለቴ ዘወትር ሓሙስና እሁድ የሚያስተላልፈውን የሬዲዮን ፕሮግራም አስመልክቶ ባካሄደው ስብሰባ ላይ የሬዲዮን ፕሮግራሙን በተመለከተ በሰፊው ተወያይቶበት ውሳኔ ሲሰጥ የለም መድኅን ወደ ኢትዮጵያ የሚሰራጭውን የሬዲዮ ፕሮግራም መጀመር የለበትም የሚል ጠንካራ ተቃውሞ የቀረበው በኮ/ል ጎሹ ወልዴ ብቻ ነበር። የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ተቃውሞም በቃለ ጉባኤ ተይዟል። ሌላው መድኅን እኤአ በጁን 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ውስጥ በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የግል እምነቴና አመለካከቴ ነው በማለት ኤርትራን እንደ አንድ ነፃ አገር የሚያውቁ መሆናቸውን በአደባባይ ላይ በግልጽ በመናገር ከመድኅን ፕሮግራም ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጋጭ የፖለቲካ መስመር የሚከተሉ መሆናቸውን በይፋ አሳወቁ። ይህ የመድኅን ሕዝባዊ ስብሰባ በካሴት የተቀረፀ ከመሆኑም ባሻገር በዚህ ስብሰባ ላይ የመኢአድ ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ተገኝተው እንደነበርም አይዘነጋም። ዛሬ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በወያኔ አስተዳደር በሕጋዊ መንገድ አስመዘገብኩት በሚሉትና ከስም ሞክሼነት በስተቀር ከመድኅን ጋር ፈጽሞ ምንም ዓይነት ግንኙነትና ተመሳሳይነት የሌለው ድርጅታቸው ከአርማው ላይ የኢትዮጵያን ካርታ አንስቶ የወያኔን ኮከብ የጨመረው ያለምክኒያት እንዳልሆነ ለሂላችንም ግልጽ ሊሆን ይገባል። እንግዲህ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ሁሉን ነገር በሚስጥር ከጨረሱና የገዢውን ፓርቲ ዋስትና ካገኙ በኋላ ነው ወደ አደባባይ ብቅ ብለው አገር ውስጥ ገብቼ በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ትግል ለማካሄድ ወስኛለሁ በማለት አዲሱን የትግል ስልት ያስተዋወቁን። ለፖለቲካ ስልጣን የማይፎካከሩትን የሙያ ማህበራትን እንኳን እውቅና ሊሰጣቸው የማይፈልገው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ኮ/ል ጎሹ ወልዴም ላቀረቡት ማመልከቻ በሥልጣን ዘመኑ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነትና ደግነት ለኮ/ል ጎሹ ወልዴ ድርጅት በምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የምስክር ወረቀት በመስጠ በሕጋዊ መንጋድ እንዲንቀሳቀሱ ፈቀደላቸው። እዚህ ላይ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ወደ ጎን እንተውና ታዲያ እንደነ ኢሠመጉ፣ኢመማ፣ኢሠማኮ እና ኢነጋማ የመሳሰሉት የሲቪክ ማህበራት ምን ኃጢያት ቢሰሩ ነው ይህ ሁሉ በደልና ግፍ በወያኔ አገዛዝ የሚደርስባቸው ብለን ስንጠይቅ መልሱን የምናገኘው ከላይ በጠቀስኳቸው ማኅበራት ስም የተፈለፈሉት ተለጣፊዎች ላይ ይሆናል።

የኢዴኃን አገር ውስጥ ገብቶ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል መወሰኑ ሊደንቀን የሚገባ አይመስለኝም። ከኢዴኃን በፊትም የተመሰረቱ የተቃዋሚ ኃይሎች ህብረቶች በሙሉ በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል መወሰናቸውንና ከአስተዳደሩ ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለመደራደር ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በተመሰረቱ ማግስት ለወያኔ አገዛዝ ያላሳወቁበት ጊዜ የለም። ሆኖም ግን ለጥሪያቸው የአቶ መለስ አገዛዝ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛነት ያሳየበት ጊዜ የለም።እስኪ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተደራጁ የሕብረብሔርና የብሔር ድርጅቶችን በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ አገናኝቶ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ልዩነቶቻቸውን በመቻቻል በኢትዮጵያ ጦርነትም ሆነ የጦርነት አደጋ በማያዳግም ሁኔታ እንዲወገድ የፓሪሱ ህብረት ከታህሳስ 9 እስከ 19 ቀን 1986 ዓ.ም በአዲስ አበባ ለሚያኪሂደው የእርቅና የሰላም ጉባዔን አስመልክቶ በጊዜው የሽግግሩ ፕሬዚደንት ለነበሩት ለዛሬው ጠቅላይ ሚ/ር ለአቶ መለስ ዜናዊ በጻፈው ደብዳቤ ካቀረባቸው አምስት ጥያቄዎች ውስጥ በተራ ቁጥር 2 ላይ የዋስትናን ጉዳይ አስመልክቶ፣

> *“... በጉባኤው ወቅት በተለይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ተወካዮች አገር የመግቢያና የመውጫ ፈቃድ (ቪዛ) ለጉባኤው ተሳታፊዎች በሞላ የደህንነት ዋስትና ና ለጉባኤውም የፀጥታ ዋስትና እንዲሰጥ፣ ... „*

ቀን፣ ህዳር 15 ቀን 1986 ዓ.ም<br>
ቁጥር፣ 24/1-4/86<br>
*ሰላምና ዕርቅ በኢትዮጵያ ጉባዔ አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ*

ጠይቀው ለጻፉት ደብዳቤ ከገዢው ፓርቲ የተሰጣቸው መልስ ከውጭ አገር ጉባሄውን ለመሳተፍ የመጡትን ፖለቲከኞች ከኤርፖርት እየተቀበለ ወደ ከርቸሌ በማጋዝ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ከዚያም በፊት አንዳንድ ድርጅቶችም ሳይቀር በግላቸው በአገር ውስጥ ገብተው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ያላቸውን ፍላጎት በተደጋጋሚ አሳውቀው ነበር። ለምሳሌ ዛሬ በወያኔ ሳይሆን በኮ/ል ጎሹ ወልዴ በጦረኝነት የሚከሰሰው የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) አገር ውስጥ ገብቶ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ያለውን ፍላጎት ሲገልጽ፣

> *“ከሌሎች ሰላምና ዲሞክራሲ ከሚሹ ኃይሎች ገር በመሆን ኢትዮጵያን ወጥረው ለያዙት አሳሳቢ ችግሮች ሰላማዊና ዘላቂ መፍትሄ ለማስገኘት በሙሉ እምነትና ቁርጠኝነት መነሳቱን ያረጋግጣል። “*

ነሓሴ 20 ቀን 1985 ዓ.ም<br>
*የመድኅን ጋዜጣዊ መግለጫ*

ብሎ ነበር። ከዚያም በተጨማሪ መድኅን በተመሰረተ ማግስት የምክር ቤት አባሉን ሳይቀር ወደ አዲስ አበባ በመላክ ፓርቲውን በሕጋዊ መንገድ ለማስመዝገብ ያደረገው ጥረት በሙሉ በወያኔ/ኢህአዴግ አስተዳደር እምቢተኝነት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም።

ሀገር ውስጥ ገብቶ ሠላማዊ ትግል ከማድረግና በምርጫ ከመሳተፍ በፊት ከአቶ መለስ አገዛዝ ጋር ድርድር ማድረግ የማይታለፍ ጉዳይ ነው። ለዚህም ዛሬ የተመቻቸ ሁኔታ ያለ ይመስላል። በአንድ በኩል ወያኔ በውስጡ በተፈጠረው መከፋፈል፣ በትግራይ ውስጥ የነበረውን ድጋፍ ማጣት፣ የባድሜ ጉዳይ፣ እያደገ የመጣው የሕዝቡ የዝምታ አመጽ...ሌሎችም በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች በተናጥል የሚያደርጉት ጉዞ የትም እንዳማያደርሳቸው ከልብ የተገነዘቡ በመሆናቸው የፈጠሩት ህብረት በሕዝብ ዘንድ እያገኘ የመጣው ድጋፍ ተደማምሮ የወያኔን አገዛዝ ለድርድር በሩን ገርበብ እንዲያደርግ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ተሟልተው የሚገኙበት ሰዓት ላይ ነው የምንጋኘው። ኢዴኃን ለጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ታህሳስ 30 ቀን 1996 ዓ.ም ቀጣዩን አገር አቀፍ ምርጫ አስመልክቶ በጻፈው ደብዳቤ ላይ የደህንነት ዋስትናን፣ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ስለማቋቋም፣የምርጫ አዋጁን፣ የሕዝብ መገናኛ ብዙሀንን አጠቃቀምና ምርጫን የሚታዘቡ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን በሚመለከት ከመንግስት ጋር ለመደራደር የሚፈልግ መሆኑን ጠቅሶ ለጻፈው ደብደቤ የወያኔ አገዛዝ በሰጠው ምላሽ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር በጽ/ቤታቸው ከህብረቱ ተወካዮች ጋር መወያየታቸውን ሁላችንም ሰምተናል።

አሁን ባለው የወያኔ አስተዳደር አሰራር ውስጥ ነፃና ግልጽ የሆነ ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ማካሄድ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። የምርጫ ሕጉ ችግር የወያኔን ሕገ መንግስት እስከ ማሻሻል ድረስ የሚወስድ ክርክር የሚያስነሳ ጉዳይ እስከመሆን ሊደርስ ይችላል። ከምርጫው ቦርድ ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ታች ወርዶ የምርጫ ጣቢያ ድረስ ያሉትን ኃላፊዎች በሙሉ በወያኔ/ኢህአዴግ እየተለመሉ የተሾሙ በመሆናቸው ተጠሪነታቸው ለሾማቸው አካል ብቻ በመሆኑ ገለልተኝነት መጠበቅ አይቻልም። ለኮ/ል ጎሹ ወልዴ የምስክር ወረቀት የሰጠው የምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ገና ለገና ለአስትዳደሩ ያለውን ታማኝነት ለመግልጽ ሲል ብቻ ከሓምሌ 19 እስከ 26 ቀን 1995 ዓ.ም በአሜሪካ ሜሪላንድ በሮክቪል ከተማ አስራ አምስት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ዴሚክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት በሚል የመሰረቱት ኅብረት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አያውቀውም ሲሉ አቶ መኮንን ወንድሙ በምርጫ ቦርድ የፖሊቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ተጠባባቂ ሬጅስትራር ለሪፖርትረ ጋዜጣ አስታውቀዋል። የመገናኛ ብዙሓን አገልግሎቱን የሚሰጠው ለበለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ለገዢው ፓርቲ በመሆኑና በውስጡም ለጋዜጠኝነት ሙያና ስነምግባር ቁብ የሌላቸው ሕሊናቸውን በሆዳቸው የቀየሩ ጋዜጠኞች የተሰበሰቡበት

በመሆኑ ብዙም የሚጠበቅበት አይደለም።ወያኔ አስቀድሞ የፈጠራቸው የራሱ የሆኑ እንደነ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ፣ የአፍሪካ ቀንድ ዲሞክራሲና ልማት...እያለ በሚጠራቸው በሲቪክ ማህበራት ስም የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ስላሉት የምርጫ ታዛቢንቱን ሚና ለእነሱ የተተው በመሆኑ ምርጫው ነጻና ገለልተኛ እንደነበርና ወያኔ/ኢህዴግም ምርጫውን በ98% እንዳሸነፈ የሚነግሩን እነዚሁ ማኅበራት ናቸው።

እንግዲህ በኮ/ል ጎሹ ወልዴና በኢዴኃኀ መሃከል ያለው ተመሳሳይነት በቃል ደረጃ በአገር ውስጥ ገብቶ በሰላማዊ መንገድ በመታገል የወያኔን አምባገነን አገዛዝ ከስሩ ነቅሎ መጣል ከሚል ቋንቋ ውጭ የተግባርና የአቀራረብ ተሳሳይነት ፈጽሞ በመሀከላቸው የለም። ኢዴኃኀ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ከአስተዳደሩ ጋር ለመደራደር የሚፈልግባቸውን ጉዳዮች በግልጽ አሳውቆ ራሱን ለድርድር አዘጋጅቷል። ኢዴኃኀ ከአስተዳደሩ ጋር የሚያደርገው ድርድር በሕዝብ ፊት ፣ በሕዝብ ስምና በአደባባይ ላይ ስለሆነ ተቃውሞአችንንም ይሁን ድጋፋችንን ለመስጠት የሚቸግረን አይመስለንም። በታህሳስ 19 ቀን 1986 ዓ.ም በማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፋይል ቁጥር 262/1303/86 መድኅን በወያኔ አቃቤ ሕግ ተከሶ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ሕዝቡን መሳሪያ ይዞ በመንግስት ላይ እንዲነሳሳ በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት እንዲነሳ ለማድረግ በሚል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/አ/ እና 252/1/ሀ/ የተጠቀሰውን በመተላለፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት እንዲነሳሳ በማድረግ በሚል ተከሰው ነበር።ታዲያ ኮ/ል ጎሹ ወልዴና ድርጅታቸው የትና? መች ነው? ከወያኔ አስተዳደር ጋር ተደራድረው ድርጅታቸው የወያኔን መልካም ፈቃድና ቡራኬ አግኝቶ እውቅና ሊያገኝ የቻለው ?! ብዙ ጥያቄዎችን ማንሳት ይቻላል። በዚህ ሕዝብ በማያውቀው ሚስጥራዊ የፖለቲካ አካሄድ ደግሞ የሕዝብን ድጋፍና ዓመኔታ ይገኛል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

... ይቀጥላል